ዴሞክራሲያ

ልዩ ዕትም ነሐሴ 2010 ዓ.ም.

## የት ደርሰናል ?

የሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ለደግም ይሁን ለክፉ ለውጥን ሲያሳይ ቆም ብለን፤ አደብ ገዝተን የት ደርሰናል ብለን መመርመር ግዴታችን ሆኖ ይገኛል። በተለይም ግርግርና ውዥንብር ሲሰፍን ከሀይ ሃይታው ፈንጠር ብሎ በጥሞና ምን እየተካሄደ ነው? ወደ የትስ እያመራን ነው? ብለን ስናጤን ምን ማድረግ እንዳለብን ግልጽ ሆኖ ይከሰታል። ታሪክ የረሳ ስህተትን ይደግማል ነውናም በተደጋጋሚ የትግላችንን ድል እየተቀማን ህዝብም ለመከራ ኢትዮጵያም ለጥፋት ስትዳረግ አይተናልና ዛሬ ሀገር አድኑን ትግል አደናቅፈው ለከፋ አደጋና የርስ በርስ ፍጅት ሊዳርጓት የተነሱትን በጊዜ መቋቋም መቻልና ሀገራችንን መጠበቅ እንዳለብን ግልጽ ነው። ዛሬ ከመቸውም ጊዜ በበለጠ ኢትዮጵያ በክፉ አደጋ ላይ ናት።

ባለፉት ሶስት አራት ዓመታት ሕዝባችን የወያኔን ከፋፍለህ ግዛ ፖለቲካ አደባይቶ በመተባበር ያካሄደው ጽኑ ትግል ወያኔን ማንገዳገዱ የሚታመን ነው። ወያኔ ከቁንጮአቸው ሞት ቀደም ብሎ ጀምሮ ውስጡ እየተናደ መምጣቱ ቢታወቅም ቀውሱ ከመጠን በላይ ሆኖበት ሊዳከም የቻለው ሕዝብ ባካሄደው መራራ ትግል ነው። ይኸው ትግል የጠየቀው መስዋዕትነት የሺዎችን ሕይወት መሆኑን መዘንጋት የለበትም። ሕዝብ ተፈጀ ሳይሆን ሕዝብ ታግሎ ለሀገሩ ተሰዋ ነው ሐቁ። ይህ መራራና ቀጣይ ሕዝባዊ ትግል የወያኔን ቀውስ አባብሶ--እርስ በርሳቸውም አናክሶ፤ ወያኔ የተጠቀመበትን ከፋፍለህ ግዛ አሸመድምዶ፤የግንጠላና የዘር ጥላቻ አቀንቃኞችን ጎራ አተራምሶ ለመሠረታዊ ለውጥ እምቢልታ ማሰማትን ጀምሮ እንደነበር ሁላችንም አይተናል። ይህ የተባበረ የሕዝብ ትግል ወደ ድል ካመራ ጥቅማቸው የሚጎዳ መሆኑን ያመኑ ክፍሎች ትግሉን ለማደናቀፍ ተረባረቡ። ወያኔ ከሚያካሂደው ጥቃት ባሻገር ኢትዮጵያን ሊገነጥሉ የሚመኙ ጠባቦች፤ በአማራው ሕዝብ ላይ ፍጅትን እውን ማድረግ ምኞታቸው የሆነ የጥላቻ አባወራዎች፤ ምዕራባውያንና ትላንትም ሆነ ዛሬ የሀገራችን ጠላት የሆኑ የአረብ መንግሥታት በየፊናቸውም ሆነ በጋራ ትግላችን ላይ ሲያሴሩ መቆየታቸውንም መካድ የሚቻል አይደለም። ወያኔ በያዘው ሊቀጥል አለመቻሉ ግልጽ ቢሆንም ሐቁን መቀበል ስላቃተው አሜሪካ ባላት መንገድ ሁሉ ወያኔዎች ላይ ጫና ማድረጉን በግልጽ ተያያዘችው። ትግሉን አደናቅፎ ወያኔ ኢሕአዴግ የተባሉትንም ማዳን የነሱ መፍትሔ እምብርትም እምቡጥም ነበርና ከመንጋው ውስጥ ይህን የማዳን ሚና በሚገባ ሊጫወቱ የሚችሉ ተፈልገው ገዱ፥ ደመቀ፥ አቢይና ለማ የሚባሉት ላይ መደምደሚያ ተደርሶ ከነዚህ ውስጥ ለአሜሪካ የሚያመችና ብቁ ሊባል የሚችል በሚል ተጠንቶ በአዲሱ የወያኔ ሹም ላይ የመጨረሻው ምርጫ ወይም ውሳኔ ላይ መደረሱ በአሁኑ ጊዜ ዓይናቸውን ላልጨፈኑ በስተቀር ለሁሉም ግልጽ ሆኖ የባዕድ ጋዜጦችም እየተቹበት ነው። በተዘጋጀው መንገድም መፍሰስ ይቻል ዘንድ ሀብታም የአረብ ሀገሮች (ሳውዲ አረቢያና የተባበሩት ኤሚሬትስም) የሂደቱ ደጋፊዎች ሆነው ቀረቡ። ቀሪው ታሪክ ነው ይላሉ ፈረንጆች።

የሕዝብ ትግል ቢያንስ በተወሰኑ አካባቢዎች ተዳፈነ፤ ቆመ። በፈረንጆቹ የተዘጋጀው የአዲሱን ሹም ሰብዕና ማሻሻጥ መርሃ ግብር በሰፊው በሥራ ላይ ውሎ ብዙዎችን ጠለፈ። የሕዝብ ትግል የደም ግብር ከፍሎ ያመጣውን ውጤት ለሹሙ ተሰጠው።የሹሙም ሃይማኖት ሚና ተሰጥቶት እስካሁንም በሥራ ላይ እየዋለ ነው። በተጨባጭ የተሠራው ጥቂት ቢሆንም፤ አንዳንዱም (ለምሳሌ እስረኛ መፍታት) በኃይለማርያም ደሳለኝም ጊዜ የተጀመረ ቢሆንም ይህ ነው የሚባል ቁምነገር በተጨባጭ፣ በመሬት ላይ ሳይሰራ ውዳሴው ለሹሙ ተዥጎደጎደ። ምንም እንኳን አዲሱ ጠቅላይ ሚኒስትር የበፊቱ ወያኔ ሲናገር ያልተሰማውን የሀገራችንን ስም ደጋግሞ ቢያነሳም፤ ወንጀል በአገዛዙ መፈጸሙን ቢያምንም፤ ለውጥ ይመጣል ቢልም ኢትዮጵያዊ ኃይሎችና ኢትዮጵያዊነትን የማዳከም ሥራ ይበልጥ እንዲቀጥል  ተደረገ። ሕዝብ ሰንደቅ ዓላማውን አክብሮና አውለብልቦ በመገኘት ብሔራዊ ስሜቱን ቢያስረግጥም ቀደም ብሎ የተዘጋጀው ኢትዮጵያዊነትን የማዳከሙ ሴራ በዚያው ልክ ተፋፍሞ እነሆ ዛሬ የግንጠላ ኃይላት ሁሉ መድረክ ያገኙበት፤ ሰንደቅ ዓላማ የሚዋረድበት፤ የግንጠላ አርማዎች የሚውለበለቡበት፤ ክርስቲያንና ቤተ ክርስቲያናት የሚቃጠሉበት፤ አማራ ጠላት ተብሎ የሚገደልበትና ፀረ አማራ ሀውልቶችን ለማቆም መሠረት የሚጣልበት ሁኔታ ላይ ደርሰናል። በወያኔና በኦሕዴድ የተወሰነ ክፍል ያለው ፉክክር እንዳለ ሆኖ በሂደቱ የወያኔ የበላይነት የተዳከመ ቢመስልም ወያኔ ስለ ጉዳዩ የመጨረሻ ቃሉን ያልሰጠ መሆኑ ለማንም ግልጽ ነው። በዚያውም የትግራይ የበላይነት ሲባል የነበረውን ሰርዞ በሕዝብ የበላይነት ባልነው መተካት ሳይሆን በሌላ ብሔር የበላይነት ለመተካት ተጨባጭ እንቅስቃሴ የሚንጸባረቅበት አካሄድም እየታየ ነው። የጥላቻ ሀውልት ሲያቆሙ የሳሉትን ካርታ ማየቱ ብቻ ይበቃል። ወያኔም ትግል ሲጀምር እነ ወልቃይት ጠገዴን ትግራይ አካል ብለው የሳሉትን የወሰኑትን የቀድሞ መስራቾቹን በአሁኑ ጊዜ ጠርቶ ማቀፉንም አይተናል። የሁኔታው ማዕከል አዲሱ ጠቅላይ ሚኒስቴርና ወዳጆቹ ለኢትዮጵያ ቀና ያስባሉ አያስቡም የሚለው ሳይሆን፤ መጠርጠር ከቶም የሚገባን መሆኑ እንዳለ ሆኖ ዋናው ቁም ነገር በተያዘው መንገድ ምን ውጤት ይኖራል የሚለው ነው ። በበኩላችን ከግምትና ግምገማ ባሻገር ፤ ለ28 ዓመት የወያኔ አመራር አባል፥ መኮንን፥ ሰላይ ሆኖ ከቆየና የአሜሪካ የስለላ ተቋም ስልጡን ከሆነ ሰው ሕዝባዊ ለውጥን ባንጠብቅም በያዘው መንገድ ግን ሳይውል ሳያድር ለውጥን ባዶ የሚያስቀር እንጂ ለውጥ የሚያመጣልን አይሆንም ከሚል ድምዳሜ ገና ከጠዋቱ የደረስንበት ነው። በጉዳዩ ያለንን ተመክሮ በባዶ ተስፋና አጓጉል አባዜ ካልሰረዝነው በስተቀር በመንግሥቱም በመለስም ሥልጣን ሲያዝ ሆ ብለው የጨፈሩ ተላሎች በሀገራችን ላይ ጉዳት አደረሱ እንጂ ይመጣል ካሉናቸው አስከፊ ሁኔታ ሊያመልጡ አልቻሉም።

ስር ነቀል ለውጥ የሚባለውን አዲሶቹ ገዢዎች አለምክንያት አልተቃወሙትም። የያዙት ጎዳና ሁሉን ሕዝብ ያሳተፈ የሽግግር ሂደትን የሚሰርዝና ያለውን የነበረውን የሚያስቀጥል በመሆኑ የሥርዓቱ መወገድ ፍላጎታቸው አልሆነም። ይህም ከራሳቸው ንግግርና ድርጊቶች ከቀሰምነው ተመክሮ ያገኘነው እንጂ መላ ምት አለመሆኑ ግልጥ ሊሆን ይገባል። የሕዝብን ፍላጎት ተጻረውም ሀገር አጥፊውን ሕገ መንግሥት ተብዬ ሰነድ እናስከብራለን፤ ኢሕአዴግም ተጠናክሮ ይቀጥላል፤ ምርጫም ያደርጋል ሲሉ ሥርዓቱን ከቀውሱ አውጥቶ ማደስ እንጂ ማስወገድ--ስር ነቀል ለውጥ ማድረግ--አለመሆኑ በገሃድ ታይቷል፤ በሹሙም በራሱ በይፋ ተነግሯል። ኢሕአዴግን ለማስቀጠልና በዚህ አጭበርባሪና ጸረ ሕዝብ ስብስብ ስርም ያው የምናውቀውን ምርጫ ለማካሄድ ሲሉ ሺዎች ውድ ሕይወታቸውን አሳልፈው አልሰጡም። በኢሕአዴግ ምርጫ አሸናፊ የሚሆነው ያው የወያኔ ሰው እንጂ ማንም ሌላ ሊሆን አይችልም። ሁሉን አቀፍ ሽግግርን ትቶ በብሔርና በሃይማኖት ማንነት ላይ መተማመን ውጤቱ አያምርም። ኢትዮጵያ ትጥፋ፤ ትገነጣጠል፤ አማራና ክርስቲያን ይታረድ ሲሉና በአደባባይ ሲለፍፉም የተሰሙት ወንጀለኞች ለፍርድ መቅረብ ሲገባቸው የክብር እንግዳ መሆናቸው መጪውን ሁኔታ የሚጠቁም ከሆነ--ይጠቁማልናም--ሀገራችን ለአስከፊ አደጋ እየተጋለጠች መሆኗ ቁልጭ ብሎ ያታያል። ከምጣዱ ወደእሳቱ እየገባ ያለውም ኢትዮጵያዊ ነን የሚለው ሕዝብ ወደ እማይታሰብ የህብረት ምርጫና ወደ መራራ ትግልም መገፋቱ ከወዲሁ

የሚታይ ነው። የኢትዮጵያ ዋና ችግር የሰፈነው ዘረኝነትና ጥበት ሆኖ መባጀቱን ካልረሳን ዛሬም ይህን ተንከባክቦ ለማስቀጠል የሚታየው አዝማሚያ ከበፊቱ በበለጠ ደም የሚያፋስስ መሆኑ አይቀሬ ነው። የተናቀውም የሕዝብ ክፍል በራስ መከላከል የሚወስደው እርምጃ ሰፊ ጉዳትን ሊያደርስ የሚችል ይሆናል። ንስሃ ያልገባን ወንጀለኛ ማቀፍ መርዙ ያልወጣለትን ዕባብ ከጉያ ማስገባት ዓይነት ነው።

ሁሉን አቀፍ የሽግግር ሂደት እውን ከሆነ ወደ መጫረሱና መፋጀቱ የጅጅጋ ጉዞ ሳንጀምር ሁሉንም ጉዳይ በሰፊና ዴሞክራሲያዊ ውይይት ለመፍታት አመቺ ሁኔታን ይፈጥራል። በአንድ ሰው ወይም ቡድን ብቻ የሚፈታ ችግር የለንምና-- ግባችን ሀገርን በጥብጦ መገንጠል እስካልሆነ ድረስ -- የጋራው ምክክርና ግብግብ እንደሚመኙልን በክላሼንና ሜንጫ ሳይሆን በጠረጴዛ ዙሪያ በዴሞክራሲያዊ ውይይት ይሆንና የብዙኀኑ አዎንታ መንገዳችንን ይቀይሳል። አዲሱ ጠቅላይ ሚኒስትር ሲናገር እንደተሰማው የሽግግር ሂደትና የሽግግር መንግሥት ምስረታ የሚለው ላይ የግንዛቤ እጥረት አለበት። የተገኘው ሁሉ ሚኒስቴር ልሁን ይላል በማለት አጉል ትርጉም ሰጥቶታል። የሽግግር ሂደት ግን በአገሪቱ የወደፊት ዕጣ ፈንታ ላይ የሕዝብን ተሳታፊነትና ወሳኝነት የሚያረጋግጥ እንጅ ለሥልጣን የሚደረግ የእሽቅድምድም መድረክ አይደለም። አዲሱ ሹም የግሉንና የቡድኑን የበላይነት አስቀድሞ ተገኝቶ ሀገራችንን ወደ ማይጠቅምና ወደማይሆን አቅጣጫ ሊወስዳት ተነስቷል። ይህን በተመለከተ ያለንን አስተያየትና ምክር በተገቢው መንገድ ብናደርስም ልንሰማ ቀርቶ ያው አሜሪካ በሰጠው ዕዝ መሠረት ድርጅታችንንም ለመከፋፈልና ለማግለል ወስነው እየተንቀሳቀሱ ነው። ሁሉም የፖለቲካ እስረኞች ሳይፈቱ ይኸው እስረኛ መፍታቱ ቆሟል ማለት ይቻላል። ለምሳሌ በጣሊያን ኤምባሲ ያሉ ሁለት አዛውንት ኢሠፓዎች ክስ ስላለባቸው አይፈቱም ሲባል በብዙ መቶ ሺ ቁጥር ለጠፋው የዜጎች ሕይወት ተጠያቂ የሆነውን አውሬ ፋሺስት ጋብዞና አግባብቶ ከስደቱ ለመመለስ ጥረቱ ታይቷል። በሕዝብ ደም ማላገጥ፤ በፍትህ ፈላጊው ላይ ሁሉ ንቀትን ማንጸባረቅ፤ የወላጅን እሮሮ አለመስማት መሆኑም ግልጽ ሆኗል። በስመ እርቅና መግባባት ጥፋቱን ያላመነውን ወንጀለኛ ማቀፍ፤ ሕዝብ የሸጠውን ቤተ መንግሥት ማስገባት፤ ...ወዘተ እየታዩ ያሉ ጸያፍ ድርጊቶች ናቸው። ከመቶ ሺ ያላነሰ ሕዝብ ደሙን የገበረለትን መሬትም በአረቦችና አሜሪካ ግፊት ተሸንፎ ለሻዕቢያ መስጠት ዘላቂ መፍትሔና ሰላምን የሚያመጣ አለመሆኑ የሚታይ ነው። ይህ የምንለው ለሕዝባችን ሰላምን ካለመፈለግ ሳይሆን ለዕውነተኛና ለዘላቂ ሰላም ካለን ጽኑ ፍላጎት ነው። የሀገርና የሕዝብን ንብረትም ለባዕድ ለመሸጥ መነሳት ለሕዝብ የሚሰጠው ጥቅም እንደሌለም ክርክር አይጠይቀንም። በሙስና የተጨማለቁ ወያኔዎችንም መልሶ መሾም ትርጉም አልባ አይደለም። ይህ ሁሉ እንዳለ ሆኖ ሕዝብን ሳያማክሩ የሚወሰዱ እርምጃዎች ጠባብ ሊባል በሚችል ሚዛን የሚደረገው ሹመትም የሚያመለክቱት ዴሞክራሲን አይደለም ።

ይህን የአዲሱን ጠቅላይ ሚኒስትር ጉዳይ ወያኔ ምላሽ ሊሰጥ በዝግጅት ላይ መሆኑም የማይታወቅ ሳይሆን የሚጠበቅ ነው። በመስከረሙ የኢሕአዴግ ስብሰባ የሚሞከረው ውጤት ካልሰጠ ውጤት ሰጪ እርምጃን ወያኔን ከመውሰድ የሚያግደው ምንም ኃይል የለም። የወያኔን እርምጃ ሊያስቆም ይችል የነበረው፣ ቀደም ሲል እንደታየውም አሽመድምዶት የነበረው የሕዝብ ትግል ነው። በአሁኑ ወቅት በሚያሳስብ ደረጃ የሕዝቡን ትግል አቀዛቅዘውታል፤ ዝም አስኝተውታል። አሜሪካ በግብጽ ሕዝብ ላይ አል ሲሲን አመጣች እንጂ ከሕዝባዊ ትግል ጎን እስከመጨረሻው አልቆመችም። በሕዝብ ድጋፍ ላይ እንጂ በባዕዳን ላይ አመኔታን መጣል መጨረሻው እንደማያምር ታሪክ ያስተማረን ሐቅ ነው። ሰርስረናቸዋል፤ ተዳክመዋል፤ ዋናዎቹ ላይም እርምጃ እስከመውሰድ ደርሰን ተዘጋጅተንም ነበር፤ በወታደር ብዛት አብዛኛው ኦሮሞና አማራ ነው፤ በስልት እናስወግዳቸውለን፤ ...ወዘተ የሚባለውን ሁሉ የወያኔ ሰላዮች ለሚመለከታቸው እንደሚያደርሱና ወንፊትነት አሁንም ሰፍኖ እንዳለ ደግሞ አንድ ሁለት ብለን ስም ቦታ ጠርተን እንድናቀርብ የሚጠብቅ ይኖራል ብለን አንገምትም። በመለስ ጊዜ የኦነግ

ጦር የተባለውን የወያኔ ሰርጎ ገቦች ከጥቅም ውጭ አውለውት መሪዎቹ የመውጫ ቪዛ ተሰጥቷቸውና መለስን በሻዕቢያ አቅራቢነት በእንባ ተሰናብተው ወደ ስደት መሄዳቸው የቅርብ ጊዜ ታሪክ ነው። ማስታወሱ ይጠቅማል፤ ወያኔን እናውቀዋለን ብሎ መናቁም ዓይጥ ሞቷን ስትሻ እንዳያስብልም መጠንቀቁ አይከፋም። በጥቅሉ ላልተለወጠና አሁንም ታጥቆ ላለ ወያኔ ሰለባ ላለመሆን ጥንቃቄ ማድረጉ ተገቢ ነው። የሕዝብን ድጋፍ መሠረት ማድረጉ፤ ሁሉን ኃይሎች ለማቀፍ በሽግግር ሂደት መጣሩ ይመረጥ የምንለውም ለዚሁ ነው። አስተማማኝና ጀርባን ማስጠጊያ መጠበቂያ የሕዝብ ተሳትፎና ድጋፍ እንጂ የወያኔ-ኢሕአዴግ ወታደሮች ወይም መሪዎች ወይም አሜሪካ አይደሉም። ሥር-ነቀል ለውጥ ያልነውም ይህን መሰል ለውጥ እየተጨናገፈ፤ ያለፈው በዚያው በመንታው እየተተካ፤ ሥርዓቱ በዋና መልኩና ይዘቱ እየቀጠለና ሕዝብ የሥልጣን ምንጭ የሆነበት መንግሥት ሳይመሠረት የሚቀጥል ሆኖ በመገኘቱም ነው። በየትኛውም ጊዜ ሕዝብ የሚፈልገው ሥር ነቀል ለውጥ በኢትዮጵያ ሙሉ በሙሉ ተካሂዶ አያውቅም። ጆሮ ያለው ይስማ! ጆሮ ያለው ይስማ !

የደረስንበት ሁኔታ በሕዝብና በወያኔ አገዛዝ መካከል ያለው መሥረታዊ ቅራኔ ገና ያልተፈታበት ነው። የሕዝብ ትግል ድል የተነጠቀበትም ነው ብንል ስህተት አይሆንም። ፍትሕ አሁንም ጠፍቷል፤ ወንጀል አደግ ሥርዓቱ ቀጥሏል ስንል በአዲስ ፈሊጥ አክራሪዎች ቂመኞች ሊሉን አዲሶቹም ሲቃጡ ተደምጠዋል። የኢትዮጵያ ሕዝብ ቂም ቢይዝ፤ በበደሉትና ግፍ በፈጸሙበት ላይ ክስ ቢመሠርት፤ ለፍርድ ይቅረቡ ቢል ሲያንሰው ነው። እንደ ሕዝብ ሊያጠፉት በተነሱት ላይ ጥላቻ ቢይዝና ዕርቅ የሚባለውም ከአንገት በላይና ጊዜ መግዣ መሆኑን ተገንዝቦ የምን ዕርቅ ቢል ምንስ ጥፋት አለው ? በለውጥ ሽፋን የተጠነሰሰው ኢትዮጵያን ሊያጠፋ የሚችል ነው ብሎ ቢጠረጥርም ተገቢ ነው። በፖለቲካ  የዋህነት ሀገርን ያሳጣል እንጂ አይጠቅምም። ዓይናችንን ከፍተን፤ ተታለን፤ በውብ ቃላት ተደናግረን፤ እንደ በግ ከአራጆቻችን እንዳንሰምር ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ አለብን። በየትኛውም የዕርቅ ማጠየቂያ ከፋሺስቱ መንግሥቱ ኃይለማርያም ጋር በሌጣው ታረቁ ሊለን የሚችል የለም። ሕዝብና ሀገርን ካጠፋው ዘረኛ ወያኔም ጋር እንዲሁ። ሃይማኖት ሌላ ፖለቲካና ይዘቱ ሌላ።

ኤርትራን አስመልክቶ የተወሰደው እርምጃ ስንፈትሽ ጠቀሜታው ለምንና ለማን ነው ብለን ስንጠይቅም፤ ሰላም ሰላም የሚባለውን በደፈናው መጻረር ስይሆን የሀገርን መሬትና የሕዝብን ደም ማክበርና አለመርሳትም ነው። በፖለቲካ እያንዳንዱ ውሳኔና እርምጃ ላይ የሕዝብ አቅዋም መንጸባረቁ አስፈላጊ ከመሆኑ በላይ ለሕዝብና ለሀገር ይጠቅማል አይጠቅምም የሚለውን ማገናዘብ ያስፈልጋል ። ስዩም መስፍን በአልጀርሱ ስምምነት ድል ተቀዳጀን ብሎ ሲቀጥፍና ሊያደናግረን ሲጥር የተፈጠረውን ሁኔታ ማስታወስ ይገባል። መሬታችንን ለሱዳን ሰጥቶ ወያኔ "በረሃ ነው፣ ... ወዘተ" ብሎ ሊያታልለን ሞክሮ እንደነበርና አሁንም ሱዳን እያደረገ ያለውን መስፋፋት የካደና የፀረ-ሰላሞች ወሬ እያለ መድረቁንም አለመርሳቱ ተገቢ ነው። ፓርቲዎችና ፖለቲከኞች (በመጥፎ ይዘቱና ትርጉሙ) ስለራሳቸው በሚለፍፉት፤ በፈጠሩት ተክለሰውነት የሚገመቱ ሳይሆን ዋናው ሥራቸው፤ እንዲሁም የሥራቸው፣ የድርጊታቸው ተጨባጭ ይዘትና አንደምታ ነው። ከጫጫታውና ከበሮ ድለቃው ባሻገር ሀቀኛውን ሁኔታ ለመረዳት ለመጨበጥ መጣሩ ይበልጥ ይመረጣል። የወልቃይት ጥያቄ የዳቦ ነው፤ የውሃ ነው የሚለን ሕዝባዊ ጥቅማችንን ከቶም የማያስጠብቅ፤ ለጥያቄያችንም ተገቢውን ምላሽ ለመስጠት ያልተዘጋጀ መሆኑን ማወቅ ይቻላል። የነወልቃይት ጥያቄ በሕዝበ ውሳኔ ይፈታ የሚሉንም የወያኔ ተጻራሪዎች ሳይሆኑ እዚያው ከወያኔ ቤተሰብ ውስጥ የሚርመሰመሱ ናቸው። ዋና ዋናዎቹን ጥያቄዎች ሳንረሳ፤ መፈክራችንንም ሳንተው፤ ሰንደቃችንንም ከትቢያ ሳንወረውር በማተባችን በእምነታችን ጸንተን መታገል ነው የኢትዮጵያዊነት ይዘቱና ትርጉሙ። ማዕከላዊ ተዘጋ ብለው መሬቱን ሊቀራመቱ ሲነሱ በደርዘን ማዕከላዊዎች በየቦታው እስረኞች ታጭቀውባቸው እንደሚገኙ መዘንጋት የለብንም። "በሬ ሆይ ሳሩን አየህና ገደሉን ሳታይ፣ ..." ሊባልብን በር መክፈትም የለብንም ፡፡

ሕዝባዊ ትግላችንን ለማደናቀፍ ሴራ ሲጎነጉንና አዋቂ ተብዬ ትውልደ ኢትዮጵያና ባዕዳንም በዋሺንግተን በርካታ ስብሰባዎች ሲያካሂዱ የተባለው ቢያንስ ለድርጅታችን ምስጢር ስላልነበረ በየጊዜው በጽሁፎቻችን ሆነ በፍኖተ አማካይነት ሴራውን ለመጠቆም ለማጋለጥ ጥረናል። ኋላም ለያዝነው አቅዋምም መነሻው ይኸው ግንዛቤያችን ነው። ሥርዓቱን (እነሱ በተለይም ጦሩን ያሉ) ለማዳን ሰው ሲመረጥና ስልጠና ሲሰጠው ጀምሮ ኢሕአፓን በተመለከተ የተያዘውን አቅዋም (ዛሬ በሥራ ላይ እየዋለ ያለውን) ምንነትም ከደረስንበት ቆይተናል። አሜሪካ በሀገራችን ላይ ያለውን ሕገ ወጥ ተጽዕኖ ተቃውመን በአብዮት ከሀገር ስላባረርነው የያዘውን ቂም አሁንም የቀጠለበት በመሆኑ ኢሕአፓን ማግለል ማራቅ ወይም ክፋፍሎ ማዳከም በሚል መርህ ሲሰራ መቆየቱ የታወቀ ነው። በዘመነ ደርግ ምንም ዓይነት ውግዘት ያላደረስንበት ቢሆንም ቂም ቂም ነው ብሎ ቀጥሏል። የኢትዮጵያን ጥቅም አሳልፈን የማንሰጥ በመሆናችንም በአያሌው እንገረብጠዋለን። የአዲሶቹን ሹሞችና የአሜሪካንን ዕቅድ ያበላሻል የተባለው ድርጅት እነሱ በሚቆጣጠሩት መገናኛ ብዙኀንም እንዳይቀርብም አዘው እንደቆሙ ያወቅነው ውሳኔ ነው። ስለ ኢሕአፓ ጥናትና ግምገማ ብሎ ጽሁፍ ያቀረበውንም ግለሰብ ማንነቱን የማናውቀው አይደለም። የምናውቀው ሻለቃና የሌሎች መሰሎቹም ሚና የኢትዮጵያዊ ሳይሆን የቅጥረኛ ነው ብለን አስረድተናል። ጊዜ ስጡ ስንባል ቀደምም ጊዜ ሰጥተን ጉድ ሆነናልና እምቢኝ ማለታችን ትክክል ነው የሚል ግምት አለን። አዲሶቹ ሹሞች ለራሳቸው ጊዜን መስጠትና በቀና ጎዳና መጓዝ አቅቷቸው ይኸው በራሳቸው ላይ መዘዝን አምጥተዋል። አቅዋማችንን የመያዝም፣ የመግለጽም መብታችንን ማንም ሊነካብን፣ ሊገድብብን ባለመፈለጋችንም ሰውየው በአምላክ የተላከልን ነው ብለው ሲቀባጥሩም አልበረገግንም። አካሄዱና ይዘቱ የሕዝብን የዴሞክራሲ ፍላጎትን ይጻረራል ስንል በአቅዋማችን ጸንተናል። መሳሳታችንንም በድርጊትና በቀና ተጨባጭ አቅዋምና እርምጃ ማሳየት ሁሉም ስላልቻሉ ወደ ስድቡና አሳፋሪ ቃላት ወርደው ማክቸልቸሉን (በፊደል ልዩነት ደም ተፋሰሱ እስከማለት) መዝቀጡን በአደባባይ አረጋግጠዋል። የሽግግር ሂደት ይኑር ሲሉ ቆይተው ሽብረክ በማለት ከሹሙ ጎን የተሰለፉትን ታዘብናቸው እንጂ እነሱን ተከትለን ትክክለኛ ሕዝባዊ አቅዋማችንን አልቀየርንም። የሚያስቀይረን ሁኔታ ካለመኖሩ ባሻገር እንዲያውም ለሀገራችን ህልውናና ለሕዝባችን ደህንነት እንድንሰጋ ተደርጓል ባይ ነን። በትግሉ ባገኘው ድል ተጠናክሮ የነበረውን ኢትዮጵያዊነት ዛሬ በፈተና ላይ እየጣሉት ያሉት እነማን እንደሆኑ ሕዝብ ሁሉ ያውቃል። የኢትዮጵያዊነትና የኢትዮጵያ ጠላቶች መሰባሰባቸውና ሰንደቃችንን ማክቸልቸላቸው አለምክንያትና ዝግጅት አይደለም። ለብሔርተኞች እየተሰጠ ያለው ቦታና እንክብካቤ ኢትዮጵያዊውን የሚያረጋጋ አይደለም። ይህንን ስንል የማንኛውም ኢትዮጵያዊ ባህሉ፣ ቋንቋው፣ ማንነቱ ለሀገራችን ኅብር ጌጥነት፤ በሀገሩ ያለው ዕኩልነትና ሙሉ መብት በማንም እንዲነካ፣ እንዲገሰስ ባለመፈለግ ጭምር ነው። ፋሺስቱን መጥራት፤ ኢትዮጵያ ከኦሮሚያ ትውጣ ባዩን፤ ... ወዘተ በክብር መጋበዙና ማዳነቁ ማንንም ሀቀኛ ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያዊ የሚያሳስብ እንጂ እሰየው የሚያሰኝ አይደለም፡፡ ኢሳያስንም ጋብዞ የታየው የስነሥርዓት ጥሰት፤ የአረቡ ልዑልም ሾፌር መሆን፤ የተከበረች ሀገርን ዝቅ አደረገ እንጂ ማንም እሰየው የሚለው አልሆነም፡፡ ዝርዝሩ ይዘቱን ጠቋሚ ነው፡፡ ሐቅን ተናግሮ ከመሸበት ያድሯል ተብሎ የለ ?

የነበረንና የያዝነውን አቅዋም በተጨባጭ ውድቅ አይሰራም ማለቱ ያቃታቸው ሁሉ ያለውን ተጨባጭ ሁኔታ--የደረስንበትን ወሳኝና ተፈታታኝ ጊዜ ሸፋፍነው-- በደፈናው የነሱ መርሃ ግብር የቆየ ነው ፤ ለአሁኑ ወቅት አይሆንም ቅስቀሳቸውንም ማንም አይደግፈውም ማለቱን መርጠዋል። ድርጅቱ በ1964 ዓ.ም. ቢመሠረትም በውቅቱ ያነሳቸው ብዙዎቹ መሠረታዊ ጥያቄዎች ምላሽ ያላገኙ መሆናቸው የሚካድ አይደለም። ምላሽ አግኝተው ባረፍን ደስተኛ በሆንም ነበር፡፡ ግን አልሆነም፡፡ የድርጅቱ መርሃ ግብርም በየጊዜው በየጉባኤው ከሁኔታዎች ጋር እንዲጣጣም ሆኖ ተሻሽሎ መቅረቡ ደግሞ የሚታወቅ ነው። መሬት ለአራሹ፤ ዴሞክራሲ ለሰፊው ሕዝብ፤ የሀገር ሉዓላዊነት ይከበር ይረጋገጥ፤ ሠርቶ አደሩ ሕዝብ መብቱ ይከበር፤ ብኄራዊ ነጋዴዎች ከበርቴዎች ይቅደሙ፤ የሴቶች ዕኩልነት ይረጋገጥ ፤ የሀገራችን ሠራዊት ሀገር ጠባቂ እንጂ የሆነ

ድርጅት መሣሪያ አይሁን፤ ዘረኝነት ይወገድ ያልነው፤ .... የቱነው ጊዜ ያለፈበት፤ ያረጀ ያፈጀ አቅዋምና ጥያቄ ? የኢሕአፓ ቅስቀሳም ሰሚ ካጣ ለምንስ ነው የአዲሱ ሹም መሥሪያ ቤት ለዓመታት ሊዘጋን ሊያፍነን የተዋደቀው ? የድርጅቱ መርሃ ግብር ይዘቱ የሕዝብ ፍላጎትና ጥያቄ ነው - ሌላ ምንም አይደለም ! አሁንም በተጨባጭ የግዳጆችን ቅደም ተከተል በመያዝ ሁሉም እስረኞች ይፈቱ፤ ፀረ ሕዝብ አዋጆች ይሻሩ፤ የሽግግር ሂደት ይጀመር እያለ ነው፡፡ የትኛው ነው ጊዜ ያለፈበት ጥያቄና አቅዋም ? ወያኔ ኢህአዴግን የሚቃወሙ አቅዋሞች ናቸው፡፡ ትክክልና ተገቢ፡፡ ወቅታዊ፡፡ ሌላ ምንስ ተጠብቆ እንደነበር ይገርመናል፡፡ ትግሉ እኮ የወያኔን ሥርዓት ለመጣል፣ ለማስውገድ እንጂ ለማደስ፣ ለመጠገን መቼም ሆኖ አያውቅም፡፡ አለ ሕዝብ ነፃ ምርጫና ፍላጎት መለስን በአዲሱ ሹም ለመተካት፤ በረከትንና ሌሎቹንም በተለጣፊዎች ተክተን ሀገር ሰላም ብለን ለመጓዝ ቅንጣትም ዓላማ ወይም ፍላጎት የለንም እንደ ሕዝብ። ሕዝብ እያለ ያለው ስር ነቀል የሥርዓት ለውጥ እኮ ነው ፡፡ የኢትዮጵያ አንድነት አለ እንጂ ሀገራችንን እንገንጥል ያለም ሕዝብ የለም፡፡ ታዲያ የገንጣዮችን መንጋ ማስቀደምን፤ ከመድረክ ላይ ማውጣት ምን አመጣው? በሆነ ምክንያት አዲሱ ጠቅላይ ሚኒስትር ባለመቻሉ ፕሬዚዳንቱ አማራን በሜንጫ ባዩን ሊቀበል ተገደደ እንጂ፡፡ በዚህ ደረጃ ሊያከብሩት የወሰኑት ኦነግ እንደሚለው የኦህዴድ ሰላይና ተላላኪ ሆኖ ጥላቻን በአማራ ላይ፤ በኢትዮጵያ ላይ ሲያሰራጭ በመከረሙ ነው? ጥያቄዎችና ጥርጣሬ ቀስቃሽ ክስተቶች ተበራክተዋል። እንታይ ጉዱ እንደሚሉት ወያኔዎች መጠየቅ መጠራጠር ሲያንሰን ነው።

የት ደርሰናል ስንል የተወሰኑ ክፍሎች ጫጫታና ግርግር ለመካፈል የተዘጋጀንበት ቦታ ላይ አንገኝም። ለመሠረታዊ የሕዝብ ጥያቄዎች ምላሽ የመስጠት ጥረት ሲደረግ እያየን አይደለንም። ሁሉም የፖለቲካ እስረኞች አልተፈቱም። ለእኛም ሆነ ለረጅም ዓመታት ለታገቱ እስረኞች የተሰጠው መልስ በህይወት ካሉም አጣርተን ይፈታሉ ከሞቱም ሀዘን እንቀመጣለን የሚል አጓጉል ምላሽ ነው - አሰራችኋቸው፣ አጠፋችኋቸው የሚባሉትና የት እንዳሉ ንገሩን፣ ፍቷቸው የሚባሉት ብርቅዬ ዜጎች፤ እህህ የሚሉ የሚያነቡ እናትና አባቶች፣ እህቶች፣ ወንድሞች፣ ልጆች፤ ጓዶችም፤ ወዳጆችም፣ ... አሏቸው። በቁስሉ ዕንጨት ስደድበት። ያልደረሰበት ግልግል ያውቃል ፤ ውድቅ ዕርቅንም ይሰብካል፡፡ አዲሶቹ ሹሞች ሁኔታውን የተቆጣጠሩ መስሏቸው ቢቧርቁም ሆነ ቢደነፉ በተጨባጭ ሥልጣን አሁንም ከወያኔ መዳፍ ተፈልቅቃ አልወጣችም፡፡ የስመኝን ግድያ ያጤኗል ! በእስር የቆዩ የወያኔ ተቃሚዎች ላይ እርምጃ መውሰድ መጀመሩን ይመለከቷል! በኢሕአፓነት ተጠርጥርው ተይዘው ለግብረ ስየል ተዳርገው የቆዩት ደብዛቸው አሁንም መጥፋቱን ያጤኗል ! ለውጥ መጥቷል ? ነገ የኢትዮጵያ አንድነት ተጠብቆ ዴምክራሲ የሚሰፍንበት ሁኔታ ተከስቷል ? ወይስ የገንጣይ መንጋ፤ የዴሞክራሲ ጠላቶች ቀን ወጥቶላቸው የኢትዮጵያ ህልውናና አንድነት ለአደጋ ተጋልጧል ? ሁሉም ኢትዮጵያዊ ለዚህ ትክክለኛውን ምላሽ መስጠት ከቻለና ከፈቀደ ክርክርና ውዝግብ አይኖርም። ሀገር ማዳን ትግሉም መቀጠል ይችላል፡፡

ጸረ ወያኔ ትግላችን ይፋፋም !

የሕዝቧ ዕኩልነትና አንድነት ለሰፈነባት ኢትዮጵያ ትግሉ ይቀጥላል !

ኢትዮጵያ በልጆቿ ተከብራ ትኖራለች !!

ሕዝብ አቸናፊ ነው !!!